የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13th Year No. 6
ADDIS ABABA 20th December, 2006

ማ ው ጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፮/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ለመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ተጨማሪ ወጪ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ.... ገጽ ፫ሺ፭፻፩

CONTENTS

Proclamation No. 506/2006

International Development Association Loan Agreement as an Additional Financing for the Second Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation .... Page 3501

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፮/፲፱፻፺፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለሁለተኛው የመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ተጨማሪ ወጪ የሚውል መጠኑ ፶፱ ሚሊዮን ፰መቶ ሺህ ኤስ.ዲ..አር (አምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ..አር) የሆነ ገንዘብ የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፯ ቀን ፪ሺ፮ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭/፩/ እና /፲፪/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "ለመንገድ ዘርፍ ልማት ድጋፍ ፕሮጀክት ተጨማሪ ወጪ የሚውል ብድር ከዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፮/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## PROCLAMATION NO. 506/2006.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE INTERNATIONAL DEVELOPMENT ASSOCIATION

**WHEREAS,** a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association stipulating that the International Development Association provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in an amount not exceeding SDR 59,800,000 (fifty nine million eight hundred thousand SDR) as an additional financing for the Second Road Sector Development Support Project, was signed in Addis Ababa on the 7th day of August 2006;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 5th day of December, 2006;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "International Development Association Loan Agreement as an Additional Financing for the Second Road Sector Development Support Project Ratification Proclamation No.506/2006."

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፪. የስምምነቱ መጽደቅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ እና በዓለም ዐቀፍ የልማት ማኅበር መካከል እ.ኤ.አ. ኦገስት ፯ ቀን ፲፱፻፺፰ በአዲስ አበባ የተፈ ረመው ቁጥር 3989-1-ET የብድር ስምምነት ፀድቋል።

## ፫ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ ሥልጣን

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስትሩ በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፶፱ ሚሊዮን ፰መቶ ሺህ ኤስ.ዲ..አር (አምሳ ዘጠኝ ሚሊዮን ስምንት መቶ ሺህ ኤስ.ዲ..አር) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

## ፬. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ ፲፩ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 2. Ratification of the Agreement

The Loan Agreement No.3989-1-ET signed in Addis Ababa on the 7th day of August 2006 between the Federal democratic Republic of Ethiopia and the International Development Association is ratified.

## 3. Power of the Minister of Finance and Economic Development

The Minister of Finance and Economic Development is hereby Empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of SDR 59,800,000 (fifty nine million eight hundred thousand SDR) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 20th day of December, 2006**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ